# የነካ ነካ ፖለቲካ

ያመረርከ እንደሆን ምረር እንደ ቅል፣

ዱባነህ ተብለህ እንዳትቀቀል፤

በሕብረተሰባች ውስጥ ንዝህላልነት ወይም ዳተኛነት ጎልቶ ይታያል፤ ራሱን፣ ትውልዱን ፣ሀገሩን ጭምር፣ለዘለቄታው ለሚጠቅሙ ጉዳዮች ላይ ያለው ተሣትፎ የቀዘቀዘ ነው። መንስዔውን ለመግለጽ በተረጋገጠ እውነት ላይ የተመሠረተ ማስረጃ የለኝም። ሆኖም በጋራም ሆነ በተናጠል ለሚመራበት፣ የፖለቲካ ሥርዐት በአሉታም ሆነ በአዎንታ ፍላጎቱን በነፃነት መግልጽ አይችልም፤ ላለፉት ሁለተ አሥርት ዓመታት በቁርጥኝነት ራሱን ገልፖ ለራሴም ለሀገሬም ይጠቅማሉ በሎ ያመነበትን ይዞ የቀጠለበት ሁኔታ ጎልቶ አልታየም፤ የታየው በአምስት ዓመት አንዴ ለሚደረገው የውሸት ምርጫ የነካ ነካ ፖለቲካ መጫወት ነው። ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶች በተለያዩ ወቅቶች ይቀርባሉ፤ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በኃይል በአንድ ዘር ስም ሀገሪቷን ተቆጣጥሯል ይላሉ፤ ተቃዋሚዎቹም አይተባበሩም፣ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት እርስ በእርሰ በመናኮር በማለት ይገልፃሉ፤

እኔ የተለየ አስተያየት አልኝ፤ በሕብረተሰባችን ውስጥ ንዝህላልነት ገዝፎል ፣ በማንኛው መስክ የምንሰራውን ሥራ አውኳል፣ የነካ የነካው ፖለቲካም የዚያ አካል ነው፤ አንደኛ፣ ለሚገጥሙን ችገሮች በግልም ሆነ በጋራ ከመቋቋም ይልቅ ራሳችንን አግለን ላለማድረጋችን በሌላው ላይ አላከን፣ ለራሳችን ግን ይቅርታ ሰናደርግ በራሳችን ላይ የጭቆናውን ሸምቀቆ ማጥበቃችንን እንዘነጋለን፤ ሁለተኛ፣ ችግሮች ሲገጥሙን ራሳችንን መቆጣጠር አቅቶን ስሜታዊ መሆናችንና ችግሩን እንዳለ ተቀብለን ለመፍትሔ ከመጣር ይልቅ አሉታዊ ኃይል እናዳብራለን፤ ሦስተኛው፣ ችግሩን መጋፈጥ ከተጀመረ በኋላ አቅማችንን በመራድና በመፍራት እናባክነዋለን፤ ሆኖም ሶስተኛው እላይ ከተገለጹት ሁለቱ የተሻለ ቢሆንም ከታሰበው ግብ አያደርስም። አራተኛው፣የሚገጥሙንን ተግዳራት ለመጋፈጥ የአእምሮ ዝግጅት አድርገን ፣ አደርገዋለሁ በሚል አዎንታዊ ኃይል ራሳችንን አሣምነን በደስታ በግልም ሆነ በጋራ ለነፃነታችን ከቆምን ጊዜ ይውሰድ እንጂ ችግሮቻችንን እናስወግዳቸዋለን። በወያኔ እስር ቤት የሚማቀቅት ጋዜጠኞች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣የፖለቲካ ተጠሪዎች ያንን ስዕብና ስላላቸው በዚያ ሰቆቃ ውስጥ ሆነው በሀገርም በውጭ ላለነው ከእስር ቤት በጹፋቸው ያስተምሩናልን።

ችግሮቻችንን ከመጋፈጥ ይልቅ ጥቃቅን ምክንያቶችን ማቅረቡ የትም አያደርሰንም፤ ለምሳሌ ወያኔን እኛ ኢትዮጵያውያን እንጠለዋለን፤ የበአዳን አገሮች ይወዱታል፤ የሀገር ሠራዊት የሚያከራያቸው አሜሪካኖች፤ የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሐብት ያለገደብ እንዲዘርፉ፣ ርካሽ፣ ሸቀጣቸውን ሕዝቡ ላይ እንዲያራግፉ የፈቀደላቸው ቻይናዎች ፤ ወሰን ቆርሶ የሰጣቸው ሱዳኖች፣ ሀገሬውን አፈናቅሎ መሬት ያከራያችው ሕንዶች፤ እንደ ባሪያ ፈንጋይ ቡቃቅላ ሴት ኢትዮጵያውያንን የሚያቀርባላችው የአርብ አገሮች ይወዱታል፤ ስለጥላቻ ትንሽ ልበል፤ ከክርስቶስ ልደት ከ3ሺ ዓመት በፊት የሥልጣኔ ጮራ በፈነጠቀባቸው፣ ሞሶፖታሚያና ግብፅ አሣማ በጣም የተጠላ ዕንሰሳ፣ ከምድረ ገጽ እንዲጠፋ የተወሰነበት ነበር፤ በሀገራችም የዕስልምና ሃይማኖት ተከታዩ አምርሮ ይጠለዋል፤ የእርሱ ዝርያ በሆነው በከርከሮ ከማለ ለእርቅ አይቀርብም፤ በኦሮሞኛ ‘ፎን ከርከሮ’ የከርከሮ ሥጋ ከተባለ ትልቅ ማህላ ነው። በኦርቶዶክ ዕምነት ተከታዩም የአሣማ ሥጋ አይበላም። በዚህ ዘመን ከቻይና እስከ አሜሪካ ከቁርስ እስከ እራት ሕዝቡ የሚመገበው አሣማ ነው።ከክርስቶሰ ልደት ከ3ሺ ዘመን በፊት እንዲጠፋ የተፈረደበት አሣማ በምግብነቱ ተወዶ ዓለም ይመገበዋል። እኛ ዛሬ ወያኔን ብንጠላውም ከቻይና እሰከ አሜሪካ ተወዳጅነት አለው፤ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በነዚህ አገሮች ለምን እንደተወደደ በአጭር አረፍተ ነገር አሰቀምጦታል፤ “የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት የቡና እግር አንቆጥርም ፤ የወታደር እግር እንቆጥራለን፤” በኦሮመኛ እንዲህ ይተረታል፤ ” ሃሬ ኪራ ገልቱ ኪራ ዱቱ ጭራ” የክራይ አህያ ከገባች ኪራዬ ከሞተችም ጭራዋ ይባላል፤ ሱማሌያ ውስጥ ተገለው ሬሣቸው ስለተጎተቱት ኢትዮጵያውያን በተቃዋሚዎች ለአቶ መለስ ዜናዊ ጥያቄ ሲቀርብለት፣’ ለማወቅ አይገባችሁም’ ነበር መልሱ።

ባጠቃላይ የፖለቲካ አካሄዳችን የነካ ነካ ፖለቲካ የሆነበት ምክንያት ወያኔን በውል ያለመረዳትና ሁለት ልብ መሆን ነው፤ ከግንቦቱ ምርጫ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ርዕዮት ዓለሙ ከአለችበት እስር ቤት ‘ነቄ ነን’ በሚለው መጣጣፏ ‘ገማሽ እርግዝና የለም፣’ እንቁርጥ የሚል ዕድምታ አለው።

ወያኔ በሙሉ ልቡ የሚያጠነጥነው አማራ ብሎ ከፈጠረው የጎሣ ፓለቲካ ዙሪያ ነው፤ በ1968 ዓ ም በደደቢት በነደፈው መረሃ-ግብር ውስጥ አማራው በትግራይ ሕዝብ ላይ ያደረሰውን በደል እንዲህ አስቀምጦታል፤የታሪክ ሥርቆት ተካሂዶብናል፣ ማንነታችንን በግድ እንድንቀይር ተደርናል፣ በመንግሥት መመሪያ እንድንቆርቁዝ ተወስኖብናል፣ ለስደት ለሴተኛ አዳሪነት ተጋልጠናል የሚሉ ሮሮዎች ናቸው፡፡እነዚህ ሮሮዎች የቀረቡት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሆነ፣ መርምሮ መፍትሄ በሰጠ ነበር።ሮሮውን አቅራቢው ወያኔ በሥልጣን ከሃያ ዓመት በላይ ቆይቶም ለሮሮው መብትሔ አላገኘም፤ አሁንም ' የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ' ነው። ይህ ለእኔ ዕንቆቅልሽ ሆኖብኛል፣ ለእናንተስ አልሆነባችሁም? ይህንን መሰል ደረቅ ርዕዮተ ዓለም ከሚያካሄድ ቡድን ጋር የሚደረግ የፖለቲካ ፊልማ በነካ ነካ ፖለቲካ ከታቀደው ግብ አይደረስም፤ ለሃያ ዓመት የታየው ያ ነው። ከመነሻው ቡዱኑ በግብተኝነት ተነሣስቶ ትግራይን ከኢትዮጵያ እገነጥላለሁ ያለ ነው። እንደህ ከሆነ አጣብቅኝ ውስጥ ከገባው ወያኔ ጋር በምርጫም ሆነ በድርድር መሠረታዊ ነገር ላየ መድረስ ይከብዳል። ስለመንደሩ ራዕይ መረሃ-ግብር ነድፎ ከሚቀሳቀስ ቡድን ጋር ተቀምጦ ሰለ ትልቋ ሀገር ችግር መፍትሔ ማግኘት እንዴት ይቻላል? በጥናት በተረጋገጠ እውነት ላይ መሠረት አድረጎ የተነሣ ቡድን አይደለም፤ እፍረቱንና ድክመቱን ከጠመንጃ ጀርባ ከልሎ፣ ከክርሰ መቃብሩ የሚወርድበትን ቀን የሚጠብቅ ነው። ቆምኩለት ለሚለው የትግራይ ሕዝብ ከአድማስ ባሻገር የሚያሳየው ተስፋና መልካም ራዕይ የለውም፤ ያመጣው በሌሎቹ ወገኖቹ መጠላትን ነው፤ ለዋሆቹ፣ ለሥልጣን ጥመኞቹ፣ ለሰው ንብረት ቋማጮቹ፣ ለሀገርና ለወገን ግድ የለሾችና ተስፈኞች፣ የወያኔ መንግሥት እንቁጣጣሽን የፈጠረላቸው ሊመስላቸው ይችላል፣ ሆኖም ግን በሰከን አእምሮ ለሚያየው የትግራይ ሕዝብ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያለያይ እንጅ ሮሮውን የሚመልስ አይደለም፤ የጥላቻን መርዝ የሚረጭ ነው።

ይህን መሰል መረዝን የሚረጭን መረሐ -ግበር ነድፎ ሀገርን የሚያስተዳድርን ቡድን በነካ ነካ ፖለቲካ ወይም ትግል አስወግዳለሁ ማለት እራስን ማታለል ነው፤ የያንዳንዱን ዜጋ እንደ አቅሙ ተሣትፎን ይጠይቃል፤ ሀገርን ከጥፋት ማዳን በሁሉም ትከሻ ላይ ያረፈ ሸክም መሆኑ ሊሰማን ይገባል፣ ለድረጅቶችና ለግለሰቦች ትቶ የራስን ነጻነት አሰቀምቶ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ወርደትን ለራስ መምረጥ ነው፤ ለቤተሰብም ለትውልድም ማፈሪያ፤ የሰው ልጅ ከገነት ወይም ከጀነት የፈጣሪውን ተዕዛዝ ባለማከበር ወደምድር ሲጣል፣ከነሙሉ ነጻነቱ ጋር መሆኑን ቅዱስ ቁራንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሰው የሃይማኖት አባቶች ይሰብካሉ፤ ሕዝብ ክርስቲያኑም ሆነ ዕስላሙ ዓምላኩ ያልነፈገውን ነፃነቱን በራሱ መሰል ሰው መብቱን አስቀምቶ መኖሩ በራሱ ኃጢያት ነው፤ የሃይማኖቶቹ ሰባኪዎቹ ሆኑ ተከታዮቹ ሙናፍቂያን ካልሆኑ በስተቀር አይቀበሉትም፤ እውነተኛው ሃይማኖት ለራስ ነፃነትና ለሌሎች መብት መከበር በእውነት መቆምን መሠረት ያደረገ መሆኑ ይታወቃል። በሌላ አንፃር ስናየው፣ አንድ ሰው በግልም ሆነ በጋራ ለራሱ ሙሉ ነፃነት ለማስከበር የሚያስከፈለውን ዋጋ ካልከፈለ ዘውትር ተዋርዶ ይኖራል፤ ሀገርም ብትሆን የያንዳንዱ ዜጋ ስዕብና የተከበረበት ምድር መሆን አለባት። ስለሆነም በነፃነት መኖርን ማንም ሊሰጠን ወይም ሊነሣን አይችልም፤ ከፈጣሪያችን የተሰጠን ጸጋ ነው ብለን የማመኑን ኃይል በአእምሮአችን እንፍጠር!

ታደለ መኩሪያ

tadele@shaw.ca